# በአፈፃፀም ዙሪያ የተጠበቁ ባህሪያት

## የትምህርት ተቋማት

1. እድሜ
2. ከለር
3. አካል ጉዳተኝነት
4. የቤተሰብ ኃላፊነቶች
5. የቤተሰብ ሁኔታ
6. የጾታ ማንነት
7. የቤት-አልባነት ሁኔታ
8. የጋብቻ ሁኔታ
9. ዜግነት/አመጣጥ
10. የግል ገጽታ
11. የፖለቲካ ትስስ ር
12. ዘር
13. ሃይማኖት
14. ጾታ
15. የወሲብ ምርጫ
16. የገቢ ምንጭ

## ሥራ

1. እድሜ
2. ቀለም
3. የብድር መረጃ
4. የአካል ጉዳተኝነት
5. የቤተሰብ ኃላፊነቶች
6. የጾታ ማንነት
7. የጄኔቲክ መረጃ
8. የቤት-አልባነት ሁኔታ
9. የጋብቻ ሁኔታ
10. ማትሪክ
11. ብሔራዊ አመጣጥ
12. የግል ገጽታ
13. የፖለቲካ ትስስ ር
14. ዘር
15. ሃይማኖት
16. ጾታ
17. የወሲብ ምርጫ
18. እንደ የቤት ውስጥ ጥቃት፣ ወሲባዊ ጥቃት ወይም አግባብ ያልሆነ መከታተል ተጎጂ ወይም የተጎጂ ቤተሰብ አባል ያለዎት ሁኔታ

## መኖሪያ ቤት

1. እድሜ
2. ቀለም
3. የአካል ጉዳተኝነት
4. የቤተሰብ ኃላፊነቶች
5. የቤተሰብ ሁኔታ
6. የጾታ ማንነት
7. የቤት-አልባነት ሁኔታ
8. የጋብቻ ሁኔታ
9. ማትሪክ
10. ዜግነት/አመጣጥ
11. የግል ገጽታ
12. የመኖሪያ ወይም የንግድ ሥራ ቦታ
13. የፖለቲካ ትስስ ር
14. ዘር
15. ሃይማኖት
16. የታሸገ የቤት መልቀቂያ መዝገብ
17. ጾታ
18. የወሲብ ምርጫ
19. የገቢ ምንጭ
20. እንደ ቤተሰብ-ውስጥ ጥቃት ተጎጂ ሁኔታ

## የሕዝብ ወይም የመንግሥት አገልግሎቶች

1. እድሜ
2. ቀለም
3. የአካል ጉዳተኝነት
4. የቤተሰብ ኃላፊነቶች
5. የቤተሰብ ሁኔታ
6. የጾታ ማንነት
7. የጄኔቲክ መረጃ
8. የቤት-አልባነት ሁኔታ
9. የጋብቻ ሁኔታ
10. ማትሪክ
11. ብሔራዊ አመጣጥ
12. የግል ገጽታ
13. የመኖሪያ ወይም የንግድ ሥራ ቦታ
14. የፖለቲካ ትስስ ር
15. ዘር
16. ሃይማኖት
17. ጾታ
18. የወሲብ ምርጫ
19. የገቢ ምንጭ

# 23 በዲሲ ሰብዓዊ መብቶች አዋጅ ስር ጥበቃ የሚደረግላቸው ባህሪያት

1. **እድሜ፥** የ18 ዓመት እድሜ ወይም ከዚያ በላይ

2. **ቀለም፥** የቆዳ ቀለም፣ የቆዳ ቀለም ላይ መለያየትን ጨምሮ

3. **የብድር መረጃ፥** የሠራተኛ የብድር-ብቁነት፣ የብድር መቋቋም፣ የብድር ችሎታ፣ የብድር ነጥብ፣ ወይም የብድር ታሪክ ላይ ማንኛውም የጽሁፍ፣ የቃል፣ ወይም ሌላ የመረጃ መግባባት።

4. **አካል ጉዳተኝነት:** አንድ ወይም ከዚያ በላይ ዋና የህይወት ተግባራትን በጉልህ የሚገድብ አካላዊ ወይም አዕምሯዊ ጉድለት፤ አካላዊ የሚባለው የመስሚያ፣ የንግግር፣ የእይታ፣ እና/ወይም የኒዩሮሎጂ ጉድለቶችን ሲያካትት አዕምሯዊ ጉድለት ደግሞ የማሰብ እና የመማር ጉድለቶችን ሊያካትት ይችላል።

5. **የቤተሰብ ኃላፊነቶች:** በህግ ጥገኝነት ወይም በደም ዝምድና ውስጥ አንድን ግለሰብ መደገፍ፣ ይህም ልጆችን፣ የልጅ ልጆችን፣ እና ወላጆችን ያካትታል፣ ግን በእነዚህ ብቻ አይወሰንም።

6. **የቤተሰብ ሁኔታ:** የ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆችን በተመለከተ ህጋዊ ሁኔታ ያላቸው እርጉዝ ግለሰብ ወይም ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ ወይም ተንከባካቢ

7. **የጾታ ማንነት:** የአንድ ግለሰብ ከጾታ ጋር የተያያዘ ማንነት፣ ገጽታ፣ መግለጫ፣ ወይም ባህሪይ፣ በልደት ጊዜ የተሰጠው የግለሰቡ ጾታ ከግምት ውስጥ ሳይገባ

8. **የጄኔቲክ መረጃ:** የአንድ ግለሰብ DNA ወይም የጄኔቲክ ቅድመ-ዝንባሌ፣ የቤተሰብ አባል የጄኔቲክ ቅድመ-ዝንባሌ፤ ከጄኔቲክ ምርመራ ጥያቄ የሚመነጭ መረጃ፣ ወይም ግለሰቡ ለበሽታ፣ ሕመም፣ ሲንድሮም ወይም ሁኔታ የመጋለጥ ቅድመ-ዝንባሌን ሊያመለክት ወይም ሊጨምር የሚችል ታሪክ

9. **የቤት-አልባነት ሁኔታ፥** ቋሚ፣ መደበኛ እና በቂ የምሽት መኖሪያ ቤት የሌለው፣ ያጣው፣ ወይም በቅርብ ጊዜ የሚያጣው ግለሰብ፣ ቤተሰብ ወይም ወጣት፣ ይህም ደህንነቱ ያልተጠበቀ አካባቢን ለማምለጥ የሚደረግ ውጤትን ሊያካትት ይችላል።

10. **የጋብቻ ሁኔታ፥** የተጋባ/ች፣ የአብሮ መኖር ግንኙነት ውስጥ ያለ/ች፣ ያላገባ/ች፣ የፈታ/ች፣ የተለያየ/ች ወይም የትዳር አጋር የሞተችበት/የሞተባት፣ እና ከእነዚህ ጋር ተያይዘው የሚመጡ የተለመዱ ሁኔታዎች፣ እርግዝና ወይም ወላጅነትን ጨምሮ

11. **ማትሪክ፥** በኮሌጅ፣ ዩኒቨርሲቲ፣ ወይም የቴክኒክ እና ሙያ ፕሮግራሞችን ጨምሮ የሆነ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ወይም ፕሮግራም ውስጥ መመዝገብ

12. **ብሔራዊ አመጣጥ፥** አንድ ግለሰብ ወይም በፊት የነበሩ ወላጆቹ የመጡበት ስቴት፣ ሀገር፣ ወይም ብሔራዊ መንግስት

13. **የግል ገጽታ፥** ውጫዊ ገጽታ፣ ፆታ እና የፆታ ማንነት ወይም አገላለጽ ምንም ይሁን ምን፣ የፀጉር አሠራር እና ቀለም፣ የፊት ፀጉር፣ ንቅሳት፣ የሰውነት መጠን ወይም ቅርፅ፣ እና የሰውነት መበሳትን ጨምሮ፣ በንግድ መስፈርቶች እና ደረጃዎች ላይ ተግባራዊ የሚሆን

14. **የመኖሪያ ወይም የንግድ ቦታ፥** የቤት ወይም የሥራ ቦታ የመሬት ላይ መገኛ

15. **የፖለቲካ ግንኙነት፥** የማንኛውም ፖለቲካ ፓርቲ አባል የመሆን ወይም የመደገፍ ሁኔታ

16. **ዘር፥** በግለሰብ የዘር አመጣጥ፣ ብሔር እና/ወይም አካላዊ ባህሪያት ላይ የተመሰረተ ምደባ ወይም ተያያዥነት

17. **ሃይማኖት፥:** ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ኃይልን ወይም አካልን የሚመለከት የግል ስብስብ ወይም ተቋማዊ የአመለካከት፣ የእምነቶች፣ እና የልምዶች ስርዓት፣ ወይም በዓለማዊ እምነቶች ውስጥ ያለው አቻ፣ ለማንኛውም እምነት የቁርጠኝነት መኖር ወይም አለመኖርን ጨምሮ።

18. **የታሸገ የቤት መልቀቂያ መዝገብ፥** በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለተወሰኑ ምክንያቶች ወይም ተከራይ መታተም አስፈላጊ መሆኑን በማሳየቱ የተነሳ የታሸገ የቤት የመልቀቂያ መዝገብ

19. **ጾታ፥** በተፈጥሮ/በባዮሎጂ ወንድ፣ ሴት ወይም የሁለት-ጾታ የመሆን ሁኔታ፣ ከእነዚህ ጋር የተያያዙ የጤና ሁኔታዎችን እና የስነ ተዋልዶ ጤና ውሳኔዎችን ጨምሮ።

20. **ወሲባዊ ዝንባሌ፥** የአንድ ግለሰብ ለሌላ ሰው(ዎች) ያለው የፍቅር እና/ወይም የወሲብ መስህብ ፤ እንደ ፍቅር፣ ሥነ ምግባራዊ ነጠላ-ጋብቻ ያልሆነ፣ ክፍት ግንኙነቶች፣ ፖሊአሞሪ፣ ወዘተ ያሉ የግንኙነት ዓይነቶችን ያጠቃልላል።

21. **የገቢ ምንጭ፥** የግለሰብ የግል እና ሙያዊ ፋይናንስ አመጣጥ፣ ከመኖሪያ ቤት ምርጫ ቫውቸሮች (ክፍል 8)፣ የአደጋ ጊዜ እርዳታ ክፍያዎች፣ የSSI ገቢ፣ ለትዳር አጋር የሚከፈል ቀለብ እና የአካል ጉዳተኝነት ጥቅማጥቅሞች ፕሮግራሞችን ጨምሮ።

22. **የቤት ውስጥ ጥቃት፥** ወሲባዊ ጥቃት፣ ወይም አግባብ ያልሆነ መከታተል (DVSOS) ተጎጂ ወይም የተጎጂ ቤተሰብ አባል የመሆን ሁኔታ፥ አንድ ግለሰብ አባል የቤት ውስጥ ጥቃት፣ ወሲባዊ ጥቃት፣ ወይም አግባብ ያልሆነ መከታተል ተጎጂ ወይም የተጎጂ ቤተሰብ አባል ሲሆን

23. **የቤተሰብ-ውስጥ ጥቃት ተጎጂ የመሆን ሁኔታ፥** የቤት ውስጥ ጥቃት፣ ወሲባዊ ጥቃት፣ ወይም አግባብ ያልሆነ መከታተል ተጎጂ የሆነ ግለሰብ፣ ቤተሰባቸው፣ ወይም የቤተሰብ አባል፣ እና/ወይም የተጎጂ እንስሳ ላይ የሚደረግ ጭካኔ